**ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ**

**Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity**

Efdpu@aol.com www.Finote.org

*ፕሮግራም፡ ረቡዕ እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰአት እስከ ሶስት ሰአት በ 25 ሜትር ባንድ*

*Programm. Wednesday and Sunday 8.00 PM — 9.00PM on 25 meter band*

***የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሀተታ***
***መስከረም 11 ቀን 2007 ዓ.ም. የተላለፈ***

## <u>የራሱን ታሪክ የላከበረ ትውልድ፤ በራሱ ላይ ይሞት በቃ እንደፈረደ ይቆጠራል !</u>

ከኢጣሊያ ፋሽስት ወረራ ማግስት የመጣው ትውልድ፤ አስተዳደጉ፤ በመልካም ሥነ ምግባርና አኩሪ ታሪክ ላይ በተመሠረተ ትምህርት ነበር። በዚህ ምክንያት ከአሁኑ ትውልድ የተለየ መስተጋብርና የታሪክ ግንዛቤ ነበረው ። የሀገሩን ታሪክ፤ ባኅል፤ ሃይማኖት፤ የነጻነት ዋጋና ክብር፤ የዐርበኞችን መሥዋዕታዊ ትግልና ጀግንነት በሚገባ ተነግሮታል። በዚህም የተነሳ፤ የሀገር ቃል -ኪዳን አክባሪነትና የወገን ፍቅር ነበረው። ለኢትዮጵያ ሀገሩ ታላቅ ቅርስ፤ ደጀንና ተስፋ ነበር ። የቀሰመውን ትምህርት እንደ መልካም አርአያ ስለሚመለከተው የሚጠበቅበትን ብሄራዊ ኃላፊነት ለመሸከም የተዘጋጀ ትውልድ እንደነበር ታሪክ ይመሰክርለታል ። ያ ትውልድ፤ በራሱ ዘመን ሦስት ሥርዐት ሲፈረራርቁ ለማየት ቢችልም ፤ በመሠረታዊ መልኩ ኢትጵያዊነቱን ጠብቆና አክብሮ የሚኖር ትውልድ መሆኑን በከፈለው መሥዋዕት አስመስክሯል ። በመርኅ ላይ የተመሰረተ ጽናቱን ጠብቆ ቆይቷል ።

የአርበኝነትን ክብርና ሞገስ፤ የነጻነትን ዋጋና ክብር፤ የሀገርና የወገን ፍቅር፤ የዓላማ ጽናትና የመርኅን ማክበር አስከባሪነት በቅጡ የተገነዘበ ኢትዮጵያዊ ትውልድ ነበር። በአንፃሩ ደግሞ፤ ይህ ትውልድ፤ የባንዳን ከሃዲነትንና ውርደት፤ የሀገር ሻጮችን ወንጀልና ጥፋት አሳፈሪነት እየተጸየፈ አድጓል። በዚህ ምክንያት፤ ጥቅመኛና እበላ ባይ አልነበረም። አመለካከቱም ከአድማስ ባሻገር ስለነበር ከብሄራዊ አስተሳሰብ ልቆ በመሄድ የዓለም አቀፍ እሴትን አንግቦ ያደገ ትውልድ እንዲሆን አድርጎታል። በመሆኑም፤ ከጎጠኝነትና ከዘረኝነት ደዌ ራሱን ያላቀቀ ሀገራዊ ራዕይ የነበረው ትውልድ ነበር። ከእርሱ ቀደም ሲል የነበረው ትውልድ፤ ለመላዋ ኢትዮጵያና ለሕዝቧ ነጻነትና ክብር ሲል እራሱን የሰዋ መሆኑን አውቆ ስለነበር፤ እርሱም ያንኑ አኩሪ ታሪክ አንግቦ በመቀጠል ፤ ለመላዋ ኢትዮጵያ ጥቅምና ብልፅግና ልማትና ሥልጣኔ፤ ደሞክራሲያዊ ሥርዐትና ፍትኅ-ርትዕ ሲል ተዋድቋል። ተሰውቷል። መክፈል ከሚገባው በላይ የህይወት ዋጋ ክፍሏል። አርበኛው ትውልድም ፤ ተተኪውን ሀገር -ወዳድ ትውልድ ተክቶ በማለፉ፤ የተከበረው አፅሙ የሠላም ዕረፍት አግኝቶ ነበር።

በወቅቱ የተዘረጋው የትምህርት ፕሮግራም፤ መማሪያ መጻህፍት፤ ሥርዐተ- ትምህርትና መምህራን ለዚያ ትውልድ ፍሪያማ አስተዋጽኦ አድርገዋል ። የትምህርቱ ጥራት፤ ከሀገሪቱ ሁኔታ ጋር የተገናዘበም ስለነበር፤ ከ1933 እስከ 1966 ዓም ደረስ የነበረው ትውልድ፤ በኢትዮጵያ ታሪክና ባኅል የበለጸገ ተራማጅ ኢትዮጵያዊ

ትውልድ ነበር። ያ ኢትዮጵያዊ ትውልድ፤ በኢትዮጵያዊ ዜግነቱ፤ የሚኮራ ስለነበር ኢትዮጵያን የሚጎዳ ተግባር ይፈጽማል ተብሎ የሚጠረጠር አልነበርም። ይልቁንም፤ የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስጠበቅ በመታገሉ፤ ከተገንጣዮችና ከአስገንጣዮች ጥቃት ደርሶበታል። የኢትዮጵያን እውነተኛ ልጃቿንና ጠላቶቿን በውል ለይቶ ያላወቀው ደርግ፤ ለሥልጣን ሲል ብቻ ያን ተራማጅ ትውልድ ሁሉ በጅምላ ጨፍጭፎቷል ። የዚህ የደርግ የጅምላ ጭፍጨፋ ቀጥታ ውጤት፤ ለኢትዮጵያ አፍራሽ ኀይሎች አመች ዕድል አግኝተው ፤ ሀገሪቱን በበለጠ ለማፍረስ በቅተዋል። ያ መሥዋዕታዊ ትውልድ፤ በይበልጥ የሚያዝነው፤ በግፍ የጨፈጨፈው ደርግ፤ ሀገሪቱን ለተገንጣይ - አስገንጣይ አሳልፎ በመስጠቱ ነበር። ምክንያቱም፤ ከፍተኛ ዋጋ ከጠየቀው ከራሱ መሥዋዕት የበለጠ የሚቆጨው የሀገሩ መጥፋት በመሆኑ ነው።

ይህንን ታሪካዊ ሀቅ ጥላሸት ለመቀባት፤ ዛሬ የሚደረገው ከንቱ ጥረት፤ የሀገራችንን ኀልውና ደብዛ ለማጥፋት ከሚደረገው ሂደት ተለይቶ የሚታይ አይደለም። ኢትዮጵያን ለማጥፋት፤ ለኢትዮጵያ ጥቅም የሚታገለውንና የቆመውን ሁሉ አስቀድሞ መምታት ስለነበረ፤ በአሁኑ ወቅት ለሀገሪቱ የሚቆረቆር ኀይል ለመዳከም ምክንያት ሆኗል። ለሥልጣን ሲባል፤ የአንድን ሀገር ትውልድ በጅምላ ማጥፋት፤ ዞሮ ዞሮ ጉዳቱ የመላው ሀገሪቱ ጉዳትና ጥፋት መሆኑን አለመገንዘብ፤ በታሪክ የሚያስጠይቅ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልግ ነበር! ይህንን የተገነዘበ ኀይል አለመኖሩ እንደ እግር እሳት ያቃጥላል ! አሁንም ከታሪክ የሚማር አልተገኘም።

የትላንቱን ታሪክ፤ ከወቅቱ ሁኔታ ጋር አገዝቦ፤ ለሀገሪቱ መፃኢ ዕድል የሚሆን ራዕይ መንደፍ ካልተቻለ፤ የሀገራችን ጉዳይ፤ ዘለዓለም በጨለማ ውስጥ ተዘፍቆ እንደሚኖር፤ ስጋታቸውን የሚገልፁ በርካታ ሀገር-ወዳድ ዜጎች አጋጥመውናል ። እኛም፤ ይህ ስጋት በቀላሉ የሚታይ እንዳልሆነ እንረዳለን።፡ የተሻለ ራዕይ ማሳየት ቀርቶ፤ መሥዋዕት የከፈለን ትውልድ ሁሉ በጅምላ እየኮነኑ መኖር፤ ለምን ዓላማ እንደሆነ መረዳት ያስቸግራል። አንዳንድ የዕድሜ ባለፀጋ የሆኑ ሽበቶ አዛውንት፤ በአጋደለ ብርዕ የሚጽፉት ከታሪክ ጋር የተጣላ አስተያየት፤ የብዙዎቹን ትዝብት አትርፎባቸዋል ። እኛ ግን፤ ከጎሊና ወቀሳ ነፃ የሚሆኑበትን ዕድል አግኝተው ታሪክን በትክክለኛው መልኩ ተመልክተው ለማስተከከል የሚያስችላቸውን እድሜ ተጎናጽፈው፤ ከታሪክ ጋር እንዲታረቁ መልካሙን ሁሉ እንመኝላቸዋለን። ያም ሆኖ፤ ታዛቢው የኢትዮጵያ ሕዝብ የመጨረሻውን ትክክለኛ ፍርድ የሚሰጥበት ቀን ግን ሩቅ እንደማይሆን አንጠራጠርም ።

ምናልባት፤ አልፎ አልፎ ከብስል ጥሬ እንዳማይታጣ ሁሉ፤ አንዳንድ አሳዳጊ የበደለው ካልሆነ በስተቀር፤ ያ ትውልድ፤ ሁሉም ለሀገሩ ሟች፤ ለወገኑ፤ ተቆርቋሪ ፤ ለመርኅ ተገዥ፤ እበላባይነትን የሚጸየፍ፤ ጥቅመኝነትን የሚንቅ እንደነበር ታሪክ ይመሰክርለታል። ከራስ ጥቅም በላይ ለሀገር ዕድገትና ልማት፤ ለሕዝብ ጥቅምና ብልጽግና ነጻነትና ዴሞክራሲያዊ መብት የታገለና የተዋደቀ ስለነበር፤ ለአላፊ-ጠፊ፤ ለከንቱ ውዳሴና ለዕለት ፍርፋሪ ሲል ባኅርዩን ላለመለወጡ፤ ከዐፄው ሥርዐት እስከ ደርግ አገዛዝና እስካሁኑ የወያኔ ዘረኛ ሥርአት ድረስ፤ ከሕዝብ ጎን

ቆሞ መታገሉ ህያው ምስክር ሆኗል ። ይህንን ሀቅ ለታሪክ መዛግብት አስረክቦ ለሀገራችን መፃዒ ዕድል ብሩኅ ተስፋ እየታገሉ ከመታገል የተለይ ምርጫ አይኖርም።፡ የታሪክን ግንዛቤ እንደ ዋልታና ማገር አንግቦ የሚታገል ትውልድ፤ የቀደምት አርበኞችንና ሰማዕታት ውለታ ሊከፍል ችለው፤ እነርሱ ያቆዩዋትን ሀገር ጠብቆ ሲያቆይ መሆኑን ያምናል። ከ 1933 እስከ 1966 ዓም የነበረው ትውልድ፤ ጀግኖች አርበኞችን እያከበረ እንዲያድግ ተድርጎ ስለነበር፤ ለኢትዮጵያ ሀገሩ፤ ለሕዝቦቿ፤ ለታሪኳና ለሰንደቅ ዓላማዋ የተለየ አክብሮትና ፍቅር ነበረው። አርበርኞችንም የሚያከብርበት " **ተጣማጅ አርበኛ** " እያለ የሚዘምረው መዝሙር ነበረው ።

**" ተጣማጅ ዐርበኛ "**

" ሠላም ሠላም ሠላም ለአፅማችሁ ፤

አርበኞች በዱር የቀራችሁ፤

መኖሪያ ሳታጡ ቤት ሳይቸግራችሁ፤

የሀገርን መዋረድ አናይም ብላችሁ፤

ለሚመጣው ትውልድ ምሳሌ ሆናችሁ፤

ሠላም ሠላም ሠላም ለአፅማችሁ ። "

ይህንን መዝሙር እየዘመረ በማደጉ ነበር ፤ የሀገርና የሕዝብ ፍቅር በአጥንቱና በህዋሱ ውስጥ ገብቶ የተክለ-ሰብዕናውንና የባኅርዩን ማንነት መግለጫ ያስረገጠው ! ለሀገሩ ሰንደቅ ዓላማ የተለየ አክብሮት እንዲኖረው በመደረጉም፤ የነፃነት ምልክቱ አድርጎ የሚቆጥራትን ዓላማ ሰንደቅ፤ ወያኔዎቹ ፤ " ብጣሽ ጨርቅ " ብለው ሲያዋርዷት በመስማቱ ፤ በትግሉ የበለጠ አምርሮ እንዲገፋበት አድርጎታል። ሀገሩን፤ ሕዝቡን ፤ ሰንደቅ ዓላማውን ፤ ታሪኩንና ባኅሉን የሚያከበር ትውልድ ስለነበረ ሁሉንም የሚያያቸው በድምሩ የማንነቱ መግለጫ ስለሆኑ ነው። ሕዝብና ሀገር የሌሎቹ ሁሉ መግለጫዎች በመሆናቸው ሀገር ከሌለ ሕዝብ፤ ሕዝብ ከሌለ ሀገር እንደማይኖር ጠንቅቆ የሚያውቅ ትውልድ፤ ለሁሉም መኖር ይዋደቃል።፡

ታላቋና ታሪካዊቷ ኢትዮጵያ ፤ ከዘመኑ ሥልጣኔ ወደኋላ በመቅረቷና ዜጎቿም በድኅነት፤ በበሽታና በጉስቆልና ውስጥ ሆነው ፍትኅ-ርትዕ ተነፍገው በደልና ጭቆና የዕለት-ዕለት ሕይወታቸው መሆኑን በመገንዘብ የለውጥ ራዕይን በማንገብ ትግል ማካሄድ አስፈላጊ ነበር ። የትግሉ ዓላማ፤ ኢትዮጵያ ከነበረችበት ኋላ ቀር ሁኔታ ለማላቅቀ ብቻ ሳይሆን፤ የጀግኖቿን አርበኞች ዉለታ ለመከፈልም ጭምር ነበር። በአሁኑ ወቅት፤ የዚህን ትውልድ ታሪክ ለማጎደፍ፤ ወያኔና ተባባሪዎቹ የሚያደርጉት ጥረት የታሪክን ሃቅ አይለውጠውም። የቀደምት

አርበኞችን ታሪክ ማክበርና ዉለታቸውንም መክፈል፤ የወቅቱ ትውልድ ኃላፊነትና ግዴታ መሆኑን መገንዝብ ያስፈልጋል። የሕዝብ ነፃነት፤ የዜጎች እኩልነትና የሀገር አንድነት ተለያይተው የሚታዩ ስላይደሉ፤ እነኝህኑ አካትቶ ለነርሱ ኅልውና መታገል አማራጭ አይኖረውም። በየትኛውም ዘመን የሚገኝ ትውልድ፤ በዚያኑ ዘመን ለሚፈፀመው መልካምም ይሁን በጎ ድርጊት ኃላፊና ተጠያቂ እንደመሆኑ፤ ከታሪክና ከትውልድ ብያኔ ሊያመልጥ አይችልም። በመሆኑም፤ ምንም ቢባል ምን፤ ከሕዝብ አስተያየት፤ ከታሪክ ፍርድም ይሁን ከትውልድ ትዝብት አያመልጥም።

ምንም እንኳን አዶልፍ ሂትለር የሰራውን ወንጀል አውቆ አስቀድሞ ራሱን በመግደሉ ምክንያት ወደ ፍርድ ሸንጎ በአካል ሊቀርብ ባይችልም፤ ስሙና ድርጊቱ በታሪክ ዘንድ የተኮነነና የተወገዘ ሆኖ ይታወሳል። ቤኒቶ ሙሶሊኒም በሰው ልጆች ላይ በፈጸመው ወንጀል ተዘቅዝቆ መሰቀሉን ታሪክ መዝግቦታል። እንደ ሂትለርና ሙሶሊኒ ተማሳሳይ ወንጀል የፈፀመው መንግሥቱ ኀይለማርያም፤ የሀገሪቱን መከላከያ ሠራዊት አጋልጦና በትኖ፤ ሀገርንና ሕዝብን ከድቶ፤ ሸሽቶ ተደብቆ ይኖራል። እስካሁንም ለፍርድ አልቀረበም። ይኽም፤ የርሱ የማምለጥና የመደበቅ ችሎታ ሳይሆን፤ እርሱን አድኖ በመያዝ ለፍርድ የማቅረብ ፍላጎት፤ ችሎታና ቁርጠኝነት የመታጣቱ ጉዳይ ይመስላል። በሰው ልጆች ላይ ጭፍጨፋ ያካሂዱ ዓለም አቀፍ ወንጀለኞችን በመያዝ ለዓለም ፍርድ ቤት እያቀረበ የሚያስፈርደውም ዓለም አቀፍ ተቋም፤ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ አሰቃቂ ወንጀልና አረመኒያዊ ጭፍጨፋ የአካሄደውን የክፍለ ዘመናችን ወንጀለኛ ለምን ዝም እንዳለው አስገራሚ እንቆቅልሽ ሆኗል ። ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት፤ ኢትዮጵያን አስመልክቶ ዝም እንዲል ያደረገውን አዚም እስካሁን ማወቅ አልተቻለም ።

ዜጋው ሁሉ እራሱን እየደለለ መኖር ካልፈለገ በስተቀር፤ ያሁኗ ኢትዮጵያ ፤ እንደ ሀገር፤ ሕዝቧም እንደ ሕዝብ ለመቆየት ከማይችሉበት ደረጃ መድረሳቸውን አምኖ መቀበል ይኖርበታል። ይህን አምኖ መቀበል፤ የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ተረድቶ ከመገንዘብ ጋር የተየያዘ ነው። ትላንት በደቡብ አፍሪቃ ሲፈጸም የነበረውን በዘር ላይ የተመሠረተውን አፓርታይድ ሥርዓት በግንባር-ቀደም ስትዋጋ የነበረችው ሀገር፤ ዛሬ ያ ድርጊት በራሷ ላይ እየተፈፀመ መሆኑን የማይገነዘብ ኢትዮጵያዊ አለ ብሎ ማመን ያስችራል። ብልሃት የመፈለጉ ዘዴ መላ-ቅጡ ጠፍቶበት ካልሆነ በስተቀር፤ ችግሩንማ ከተገነዘበው ቆይቷል። የሀገሩን ችግር ተረድቶ መፍትሄ የማያመጣ ትውልድ፤ ግን ራሱን እየኮነነ እንደሚኖር ማወቅ አለበት ። ዝንተ-ዓለም ስለ ችግር እየተብተከተኩ መኖር ከችግር አያወጣም ። የሀገርን ችግር ለማስወገድ፤ እያንዳንዱ ዜጋ አንድ አንድ ጠጠር እንዲወረውር ይጠበቅበታል።

የኢትዮጵያ አካል የነበረውን ሕዝብና መሬት በብጣሽ ማስታዎሻ ፈርሞ ከማባረር ጀምሮ፤ በብዙ መቶ ኪሎ ሜትር የሚለካውን የሀገራችንን ምዕራብ ግዛት ለባዕድ መንግሥት ያስረከበ የትግራይ ወያኔ ቡድን፤ የኢትዮጵያን ቅርፅ ከዓለም ካርታ ላይ በመደምሰስ ላይ መሆኑን የማይገነዘብ ኢትዮጵያዊ በአሁኑ ወቅት አለ ብሎ ማመን ያስቸግራል። የኢትዮጵያ ግዛት አንድነትና ሀገራዊ ልዕልና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸረሸረ መሄዱን የማይረዳ

ኢትዮጵያዊ ሊኖር አይችልም ። የሀገራችን ጠርፍና ድንበር ጃርት እንደበላው ዱባ እየተፍረከረከ መሄዱን የማያይ ኢትዮጵያዊ ይኖራል ተብሎ አይታሰብም !

በቅኝ ግዛት ሲማቅቁ ለነበሩት የአፍሪካ ሀገሮች ነጻነት ስትከራከር የነበረች ሀገር፤ ዛሬ የራሷ ጎለውና በጥያቄ ውስጥ ሲገባ አፍሪካውያኑ፤ ምን ሊሰማቸው እንደሚችል ለመገመት ባይቻልም፤ አንዳንዶቹ እንደሚሳለቁባት ግን መጠርጠር እንችላለን። የዓለም ፖለቲካ፤ ከዘማዊነት የማይላቀቅ መሆኑን ስለምንረዳ ይህ ቢሆን አያስደንቅንም ። የሀገርን ጥቅም ማስጠበቅ ቀርቶ፤ አንደ ሸቀጥ ዕቃ ሀገርን በገንዘብ መቸብቸብ በኢትዮጵያ ታሪክ፤ የትግራዩ ወያኔ የመጀመሪያው ሁኗል ።

ታሪክን ታሪክ ያማጠዋል እንዲሉ ፤ በ 19ኛው ክፍለ-ዘመን መገባደጃ ላይ ፤ የኢትዮጵያ ግዛት አካል የነበረውን የአሰብን መሬትና ወደብ ፤ ሡልጣን ኢብራሄም የተሰኘ የአካባቢው ነጋዴ ፤ ጆሴፐ ሳፔቶ በሚል ስም ለሚታወቅ ኢጣሊያዊ የሃይማኖት ሰባኪና ነጋዴ ፤ በገንዘብ ሸጦለታል። የዚያን ዘመን የሀገር ክኅደት ጠንቁ ለዛሬው ትውልድ ተርፏል፡፡ ታዲያ ፤ ዛሬ ወያኔ ተመሳሳይ ክኅደት ቢፈጽም ምን ያስገርማል ካልተባለ በስተቀር፤ እናም ደግሞ፤ የሀገሩ ቀስ በቀስ እየጠፋችና እየተሸጠች መሄዷን ተገንዝቦ ሁሉም ሆ ! ብሎ በመነሳት ሀገሩን ከጥፋት ማዳን ካልቻለ፤ ኢትዮጵያን ማንም መጥቶ ሊያድናት እንደማይችል ማወቅ አለበት ።

በታሪኳ የአናብስት ሀገር ተብላ ስትጠራ የነበረች ሀገራችን ኢትዮጵያ፤ አናብስቷ ሁሉ ክንዳቸውን በመንተራሳቸው ምክንያት፤ ጃርቶች የሚፈነጩባት ሀገር ሆናለች። ያም ቢሆን ግን፤ የኢትዮጵያን ትንሣኤ ለማምጣት የሚዋደቁላት ጀግኖች እንዳሉ መታወቅ አለበት። የጊዜው የሀገራችን ሁኔታ የጨለመ ሊመስል ይችል ይሆናል። ግን የሀገራችንን ትንሣኤ -ብሥራት ለመስማት ጊዜው ሩቅ እንደማይሆን ዜጎቿ ሁሉ ያምናሉ። በእርግጥም የሀገራችን መጻዒ ዕድል ብሩኅ ተስፋ ይዞ እንደሚመጣ ጥርጥር አይኖርም። ዕእነትን ተጨባጭ ለማድረግ ግን ሁሉም የየበኩሉን ድርሻ መውጣት የግድ ነው ። ሥርዔት ያለመሥዋዕት እንደማይገኝ ሁሉ፤ ውጤትም ያለ ብርቱ ጥረት- ግረት አይመጣም። የሀገራችን መከራ እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ቤተሰብ ደጃፍ እንዳንኳኳ ሁሉ፤ ከመከራው ለመላቀቅ ደግሞ እያንዳንዱ ቤተሰብ የድርሻውን እንዲወጣ ይጠብቅበታል ።

በዓለም ታሪክ ሂደት ፤ በተለያዩ ምክንያቶች፤ በሰው ልጆች ላይ የተለያዩ ወንጀሎች ተፈጽመዋል። በስመ-ሥልጣኔ፤ ሃይማኖት፤ ዴሞክራሲ፤ ሶሻሊዝምና አብዮት እልቂት ተካሄደዋል። ሀገር ለማቅናት ሲባልም ብዙ ግፍና በደል፤ ግድያና ጭፍጨፋ ተፈጽሟል ። ኢሰብዓዊ ወንጀሎች ተደርገዋል። በ " ነፃነት ትግል " ስም ፤ አያሌ ንጹሃን ዜጎች ተረሽነዋል ። በመደብ ትግል ሳቢያም አረጋውያን፤ ሴቶችና ህጻናት በህይወታቸው በእሳት ተቃጥለዋል። የሰው ልጆች ደም እንደጎርፍ ፈስሟል። የሰዎች አጽም በየጦር ሜዳዎች ወድቆ ቀርቷል። የኢትዮጵያ ሕዝብም፤ የእልቂቱ ሁሉ ገፈት ቀማሽ ነበር። አሁንም እልቂቱ ቀጥሏል። በተለይም በሃያኛው ምዕተ ዓመት መገባደጃ የተፈጸመውና በሃያ አንደኛው ምዕተ ዓመት መግቢያ ጀምሮ የቀጠለው የኢትዮጵያን ሕዝብ

መከራና ስቃይ መዘርዘር የሚቻል አይደለም። የሀገራችን ሕዝብ መከራና ስቃይ የሚያበቃበትን ቀን በጉጉት እንናፍቃለን። ናፍቆታችንን ለመወጣት ግን፤ ለትግል ያለነን ቁርጠኝነትና እየጎመዘዘ የሚሄደውን መሥዋዕትነት አቀናጅተን መጓዛችንን በማረጋገጥ ይሆናል ። የኢትዮጵያን ሕዝብ ሠላም የነሱ ሁሉ፤ እነርሱም ሠላምን አያገኟትም። " ሠላም ነህ? ሠላም ነሽ ? ስእተባለ ብቻ ሠላም አይወርድም። ሠላም እንዲመጣ ከተፈለገ፤ ፍትኅ-ርትዕ መስፈን አለበት ። ሕዝብም ነፃነትን መጎናፀፍ ይኖርበታል ። ያ እስካልሆነ ድረስ ሠላም አይመጣም ።

**ትግላችንን ለማዳከም ብቻ ሳይሆን፤ ልሣናችንንም ለመዝጋት፤ በተጻራሪዎቻችንን በኩል የሚደረገውን ሙከራ ሁሉ እንደ አመጣጡ የማክሸፍ ብቃታችንን ማንም ሊጠራጠር አይችልም። ለማንኛውም ጥቃት አንበረከክም ማለት፤ አልተቸነፍንም ማለት ብቻ ሳይሆን፤ ችንፈት የሚባለው ቃል ራሱ ፤ በእኛ መዝገበ-ቃላት ውስጥ የማይታዎቅ መሆኑንም ለመግለጽም ጭምር ነው።** ድል ማለት ከመንግሥት ሥልጣን አያያዝ ጋር ብቻ እንደሆነ የሚቆጥሩ ግብዞች እንዳሉ እናውቃለን ። እኛ ችንፈት ብለን የምንቆጥረው፤ የተነሱበትን ዓላማ ሸጦ፤ የገቡትን የትግል ቃል- ኪዳን አርክሶ፤ ሕዝብንና ሀገርን ከድቶ፤ ለአምባገነኖች ተንበርክኮና ተረግጦ መገዛትን ነው። ኢትዮጵያዊነትን አዋርዶ፤ የባዕዳንን ጥቅም ለማስጠብቅ ብቻ ሲባል እራስን አዋርዶ የሚመጣ የመንግሥት ሥልጣን እንደ አቸናፊነት ከተቆጠረ፤ በአፍንጫችን ይውጣ! ለአምባገነኖች አንበረከክም የሚለው ስንደቅ፤ የትግላችን አልፋ - ዖሜጋ በመሆኑ፤ አስተምሮ ካሳደገን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ቆመን መከራውንና ግፉን መካፈላችን፤ የአቸናፊነት ምልክታችን ነው። በታሪክ ፊት አሳፋሪ ሥራ ሰርቶ በምንሊክ ግቢ ውስጥ መገኘት፤ ከተነሳንበት ዓላማ ጋር ተጻጻሪ በመሆኑ፤ የታሪክ አቸናፊነትን ተጎናጽፈን ትግላችንን እንቀጥላለን ። ሀገራችንም ከዘርኞች ሥርዐት ነፃ ትወጣለች ! ለዘለዐለምም ትኖራለች !

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች!